# «የፐራይቬታይዜሽን»፣ የእርሻ ሚሊየነሮች!!!
## «ወርቅ የምትወልደውን ዝይ ገደልናት!!!»
## (ክፍል አንድ)

ፀ/ት ፂዮን ዘማርያም

በመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (PRIVATIZATION AND PUBLIC ENTERPRISES SUPERVISING AGENCY) ባለፈው 26 አመታት ከ365 መንግስታዊ ድርጅቶች በላይ ወደ «ግል ዘርፍ» አዘዋውሮል!!! ከ1986 ዓም ድረስ ከመንግሥት ይዞታ ወደ «ግል ይዞታ» ከተዛወሩ የልማት ድርጅቶች 3.3 ቢሊዮን ብር ተገኝቶል:: ከ1997 ዓ/ም እስከ 2006 ዓ/ም ድረስ ደግሞ 15 ቢሊዮን ብር ተገኝቶል፡፡ በድምሩ 18.3 ቢሊዮን ብር ከሽያጩ ተገኝቶል፡፡ «መንግሥት ከሸጣቸው የልማት ድርጅቶች ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ ዕዳ አልተከፈለም» የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ሚድሮክ ኢትዮጵያ 2 ቢሊዮን ብር ባለዕዳ ነው፡፡

የፐራይቬታይዤሽን ዋና ዓላማዎች አንኳሩ የመንግሥትን ጣልቃ ገብነት በኢኮኖሚው አምራች ዘርፍ ውስጥ ለመቀነስ ሲሆን፣ በዚህም መንግሥታዊው ዘርፍ ውስን የሆኑ ወይም ቁጥብ የሆኑ የተፈጥሮ ኃብቶችን አጠቃቀም በተሸለ ምርታማ ሁኔታ በመቀየር ድህነትን የማጥፋት መርሃ-ግብር ለመንደፍ ነው፡፡ በኢትጵያ የተከናወነው የፐራይቬታይዜሽን መርሃግብር ግን የመንግሥታዊውን ዘርፍ ገቢ ምንጭ አደጋ ላይ በመጣል ለጥቂት የአንባገነን መንግሥትና ጥቂት ከበርቴ ግብረአበሮቻቸውን ለመጥቀም በርካሽ ዋጋ የመንግሥት እርሻዎችን በመሸጥ የሜድሮክና መሰል ከበርቴዎች የገቢ ምንጫቸውን በማሳደግ የሀገር ኢኮኖሚን እንዳደቀቁ ይታመናል፡፡ «The purpose of privatization is to limit the involvement of government in the productive sector of the economy so that it makes public sector reforms to relieve scarce resources and re-deploy them to higher priority poverty reduction programs. In the case of Ethiopia the government has undertaken privatization programs at the risk of consolidating the state owned enterprises in the hand of few oligarchs. » By Ezana Kebede, August 19, 2014

መንግስት ወደ ግል ዘርፍ እንዲዘዋወሩ የወሰናቸውን እርሻዎች፣ ፋብሪካዎችና የማዕድን ኃብት ወዘተ እሚገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታ የምጣኔ ሃብት፣ የቴክኒክና የገንዘብና የመሸጫ ዋጋ ተመን በጥልቅ ጥናት ላይ በመመስረት ለጨረታ ማቅረብ፣ ድርጅቶቹን ያሉበትን ሁኔታ፤ ዝርዝር የሰው ሃይል መረጃዎችን፣ ንብረቶችን፣ መዋዕለ ንዋይና የህግ ሁኔታ ከመሸጣቸው በፊት በጥልቀት የማጥናት ሃላፊነት እንዳለባቸው ቢታወቅም ብዙዎቹ አትራፊ የነበሩ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የነበራቸውን በብዙ ሚሊዮን ብር የሚደርስ ተቀማጭ ገንዘብ ባለሃብቱ ድርጅቱን በገዛ ማግስት ገንዘቡን ወደ ግል አከውንቱ በማዘዋወር ድርጅቶቹን በነፃ የተረከቡ ባለሃብቶች እንደነበሩ ማሰረጃዎቹ በጥናት ያረጋግጣሉ፡፡ «The government should privatize these large companies, if only it identifies operational inefficiencies, to have a better management, technology transfer and transparency. Even then, it could privatize a portion of these public firms only to add value, and not to be sold to single investor, but to the general public. »

በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመን፣ በመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በደርግ አገዛዝ ስርዓት የተወረሱ መንግስታዊ ድርጅቶችን ወደ ግሉ ዘርፍ ለማዘዋወር በ1994 ዓ/ም በአዋጅ የተቆቆመ ድርጅት ዴሬክተር ጀነራል አሰፋ አብርሃ (ስዬ አብርሃ ወንድም) አትራፊ የመንግሥት እርሻዎችን ወደ ግል ዘርፍ አዘዋውረዋል፡፡

የመንግስት እርሻዎች ኢንተርፐራይዝ ከ1994/95 እስከ 2003 ፐራይቬታይዝ የተደረጉ
(List of Privatized Stat Owned Enterprises from 1994/95 up to March 2003)

{1} ሙሉ ዴሪ ፋርም የመንግስት እርሻ በ2/10/2000ዓ/ም፣ ገዢ አቶ አብደላ ናስር የተሸጠበት ዋጋ 4,013,003.00 ሚሊዩን ብር

{2} ሰላሌ ዴሪ ፋርም ቁጥር 2ና3 የመንግስት እርሻ በ10/6/2000 ዓ/ም፣ለጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ የተሸጠበት ዋጋ 1,200,000 ሚሊዩን ብር

{3} ሞጆ ዴሪ ፋርም የመንግስት እርሻ በ8/18/2000 ዓ/ም፣ ገዢ አቶ አቶ አየለ ወልደሰንበት የተሸጠበት ዋጋ 2,620,656 ሚሊዩን ብር

{4} ጎጃም ጎንደር አግሪካልቸራል ኢንተርፐራይዝ፣አየሁ ሎወር ኤንድ አፐር፣ብር ፋርም (4 ፋርምስ) የመንግስት እርሻ በ7/7/2000 ዓ/ም፣ ለኢትዮ-ኮፊ ኤንድ ፕላንቴሽን ኤንድ ማርኬት ቲ ፒኤልሲ የተሸጠበት ዋጋ 103,750,000 ሚሊዩን ብር

{5} ውሽ ውሽ ጉመሮ የሻይ ተክል እርሻ፣ የሻይ ምረት ኤንድ ማርኬት ኢንተርፐራይዝ (3 ፋርም) የመንግስት እርሻ በ7/7/2000 ዓ/ም ፣ ገዢ ኢትዩ-ኮፊ ኤንድ ቲ ፕላንቴሽን ኤንድ ማርኬት ፒኤልሲ የተሸጠበት ዋጋ 222,695,938 ሚሊዩን ብር

{6} ኩሪፍቱ ዴሪ ፋርም የመንግስት እርሻ በ3/15/2000 ዓ/ም፣ለፉአንግ ቢውልዲንግ ኮንትራክተር የተሸጠበት ዋጋ 1,800,000 ሚሊዩን ብር

{7} ቢሸፍቱ ፋርም የመንግስት እርሻ በ7/2/1998 ዓ/ም፣ ገዢ አቶ አማኑኤል አሰፋ የተሸጠበት ዋጋ 250,900 ሽህ ብር

{8} ደብረ ዘይት ዴሪ ፋርም የመንግስት እርሻ በ3/4/2000 ዓ/ም ፣ ገዢ አቶ ሃይለ ልዑል ተክለማሪያም የተሸጠበት ዋጋ 750,000 ሽህ ብር

{9} መናገሻ ዴሪ ፋርም የመንግስት እርሻ በ9/3/1999 ዓ/ም፣ ገዢ ፍሎራ አግሪካልቸር የተሸጠበት ዋጋ 515,645.30 ሽህ ብር

{10} ጨፌ ፋርም የመንግስት እርሻ በ1/8/1998 ዓ/ም፣ ገዢ ሜድሮክ የተሸጠበት ዋጋ 8,027,302.23 ሚሊዩን ብር

{11} ላይፍ ስቶክ ማርኬት የመንግስት እርሻ በ1/8/1998 ዓ/ም፣ ገዢ ሜድሮክ የተሸጠበት ዋጋ 74,778,978.10 ሚሊዩን

ብር
{12} <u>ኩምቢ ዴሪ ፋርም</u> የመንግስት እርሻ በ3/27/1999 ዓ/ም፣ ገዢ ወ/ሮ ማርታ ከበደ የተሸጠበት ዋጋ 8,056.09 ሽህ ብር
{13} <u>ጂማ ዴሪ ፋርም</u> የመንግስት እርሻ በ9/13/1999 ዓ/ም፣ ገዢ ቪዝን አግሪና አግሮ ኢንዱስትሪ የተሸጠበት ዋጋ 800,000 ሽህ ብር
{14} <u>ጎንደር ዴሪ ፋርም</u> የመንግስት እርሻ በ9/13/1999 ዓ/ም፣ ገዢ ወ/ሮ ገዳሪፍ ውብነህ የተሸጠበት ዋጋ 730,000 ሽህ ብር
{15} <u>የዶሮ ርቢና አዲስ ፕሮጀክት</u> ጨምሮ የመንግስት እርሻ በ1/8/1998 ዓ/ም፣ገዢ ሜድሮክ የተሸጠበት ዋጋ 144,177,665.10 ሚሊዩን ብር
{16} <u>ሆለታ ዴሪ ፋርም</u> የመንግስት እርሻ በ10/25/1999 ዓ/ም፣ገዢ የግብርና ሚንስትር የተሸጠበት ዋጋ 2,917,296.55 ሚሊዩን ብር
{17} <u>አልማ ዴሪ ፋርም</u> የመንግስት እርሻ በ4/12/2001 ዓ/ም፣ ገዢ ባዝን ፒኤልሲየተሸጠበት ዋጋ 1,200,000 ሚሊዩን ብር
{18} <u>ረፒ ዴሪ ፋርም</u> የመንግስት እርሻ በ3/5/2001 ዓ/ም፣ ገዢ ለኔ ጀነራል ቢዝነስ ፒኤልሲ የተሸጠበት ዋጋ 5,280,000 ሚሊዩን ብር
{19} <u>መካከለኛ አዋሽ</u> የመንግስት እርሻ ቀንና ዓ/ም ያልተጠቀሰ፣ ገዢ ላራም ካፊ ኢትዩ ሌኮች የተሸጠበት ዋጋ 2,832,242.61 ሚሊዩን ብር
{20} <u>ዲቨሎፕመንት ስቶር</u> የመንግስት እርሻ ቀን ያልተጠቀሰ፣ለአግሪ ሪስርች ዲቨሎፕመንት የተሸጠበት ዋጋ 2,212,549.40 ሚሊዩን ብር

ከ1994/95 እስከ 2003 ዓ/ም ሃያ የመንግስት እርሻዎች ኢንተርፕራየዝ ወደ ግሉ ዘርፍ በፕራይቬታይዝ መርሃ ግብር በ580 ሚሊዩን 560 ሽህ 232 ብር ሽያጪ ያዘዋወረ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ አምስት እርሻዎች በ553 ሚሊዩን 429 ሽህ 883 ብር በመግዛት፣ ማለትም 95 በመቶ ድርሻ የገዙት ሼክ መሃመድ በኃብት ላይ ኃብት ተንበሸብሸዋል፡፡
{1} ጎጃም ጎንደር አግሪካልቸራል ኢንተርፕራይዝ፣አየሁ ሎወር ኤንድ አፐር፣ብር ፋርም (4 ፋርምሰ) የመንግስት እርሻ በ7/7/2000 ዓ/ም፣ለኢትዩ-ኮፊ ኤንድ ፕላንቴሽን ኤንድ ማርኬት ቲ ፒኤልሲ የተሸጠበት ዋጋ 103,750,000.00 ሚሊዩን ብር (2) ውሽ ውሽ ጉመሮ የሻይ ተክል እርሻ፣የሻይ ምረትና ገበያ ኢንተርፕራይዝ ሦስት እርሻዎች፣ በ7/7/2000ዓ/ም ውል በተፈጸመበት ቀን፣ ለኢትዩ-ኮፊ ኤንድ ቲ ፕላንቴሽን ኤንድ ማርኬት ፒኤልሲ 222,695,938.00 ሚሊዩን ብር ተሸጠ፡፡ (3) ጨፌ ፋርም፣በ1/8/1998ዓ/ም ውል በተፈጸመበት ቀን ለሜድሮክ 8,027,302.23 ሚሊዩን ብር ተሸጠ፡፡ (4) ላይፍ ስቶክ ማርኬት፣በ1/8/1998ዓ/ም ውል በተፈጸመበት ቀን ለሜድሮክ 74,778,978.10 ሚሊዩን ብር ተሸጠ፡፡ (5) የዶሮ ርቢና አዲስ ፕሮጀክት ጨምሮ፣ በ1/8/1998ዓ/ም ውል በተፈጸመበት ቀን ለ ሜድሮክ 144,177,665.10 ሚሊዩን ብር ለሼክ መሃመድ ተሸጠ፡፡

<u>አግሪ-ሲፍት ኢትዩጵያ</u> ***Agri-Ceft Ethiopia*** አግሪ-ሲፍት ኢትዩጵያ የተመሠረተውና ሥራውን የጀመረው በ2005 እኤአ ሲሆን ቡና በማልማትና ወደ ውጪ በመላክ ተግባር ተሰማርቶል፡፡ በ2007እኤአ በመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በኩል ለሸክ መሃመድ ሁሴን አሊ አልአሙዲ የተለያዩ የመንግስት እርሻዎች የነበሩ የእህል፣ የበቆሎ፣ የጥራጥሬና የቡናና ሻይ ልማት እርሻዎች ተሸጡላቸው፡፡ በእነዚህ እርሻዎች ውስጥ ሁለት የሻይ ልማት እርሻ፣ የቡና እርሻ፣ የአበባ እርሻ፣ የጥራጥሬና የፍራፍሬና አትክልት እርሻዎች ልማት ሥራ ላይ፣ 2400 ቆሚ ሠራተኛና 18000 ግዚያዊ የስራ እድል አግኝተዋል፡፡ በ2007/08 እኤአ አግሪ-ሲፍት ኢትዩጵያ 20.6 ሚሊዩን ዶላር ዓመታዊ የገንዘብ ዝውውር ማድረጉን ሪፖርት አድርጓል፡፡***Agri-Ceft.*** *Agri-Ceft Ethiopia was established and started its operation in 2005 by producing and exporting coffee. In 2007, it acquired various state-owned grain farms and tea plantations and started producing and marketing maize and tea. It employs about 2,400 permanent employees and up to 18,000 daily labourers. Agri-Ceft is planning to start producing essential oils for the export market. The firm had a reported annual turnover of $20.6m in FY2007/08.*የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ <u>ዴሬክተር ጀነራል በየነ ገብረመስቀል</u> ዘመነ ሥልጣን በደርግ መንግሥት የተወረሱና በጣም አትራፊና በውጪ ምንዛሪ ከ250 እስከ 300 ሚሊዩን ዶላር ለሃገሪቱ ይደጉሙ የነበሩ የመንግሥት እርሻዎች ወደ «ግል ዘርፍ» የተላለፉት መኃል:-

<u>ሆሪዘን ፕላንቴሽን ፒኤልሲ</u>፣(HORIZON Plantations PLC) ለሜድሮክ ካንፓኒ የተሸጡ የቡና እርሻዎች ውስጥ፤
{1} <u>የላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንደስትሪ</u> (Upper Awash Agro-Industry) እርሻ ልማት በ860 ሚሊዩን ብር፣
{2} <u>ቡና ማደራጃና ማከማቻ</u> (Coffee Processing & Warehouse Enterprise) እርሻ ልማት በ228.2 ሚሊዩን ብር፣
{3} <u>ጎጀብ እርሻ ልማት</u> (Gojeb Farm) እርሻ ልማት 35.1 ሚሊዩን ብር፣በአጠቃላይ የሜድሮክ ባለቤት ሼክ አላሙዲና የፕራይቬታይዜሽን ኃላፊ በየነ ገብረመስቀል 1 ቢሊዩን 123 ሚሊዩን ብር አትራፊ የሆኑ የቡና እርሻዎችና የውጭ ምንዛሪ ያስገኙ የነበሩ የህዝብ ንብረቶችን ለሼክ አላሙዲ ሸጠዋል፡፡ «ሚድሮክ በላይኛው አዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪና የቡና ማዘጋጃ ስም ያለበትን 1.1 ቢሊዩን ብር ዕዳ እስካሁን እንዳልከፈለ ሥራ አስኪያጁ አቶ ይበልጣል ሽመልስ ገልጸዋል፡፡» አዲስ ዘመን ጋዜጣ መጋቢት 20 ቀን 2009ዓ/ም
የህወሃት የጦር አበጋዞች መንግስት፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የቡና እርሻዎችን ሸጦ የስካሪር ኮርፖሬሽን በማቆቆም አስር የሸንኮራ አገዳ እርሻ ልማቶች አርሶ አደሮችን ከመሬታቸው ላይ አፈናቅለዋል፡፡ የስካEC ፋብሪካዎች የመገንቢያ ወጪ 77 ቢሊዩን ብር በሜቴክ ተዘርፎል፡፡
በኢትዩጵያ ሙስና የተፈበረከው በመለስ ዜናዊ ህወኃት አገዛዝ ዘመን፣በመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (PRIVATIZATION (BRIBE-VATIZATION) AND PUBLIC ENTERPRISES SUPERVISING AGENCY*)* ተቋም

ነበር፡፡ የኢትዩጵያ ህዝብ ‹‹ወርቅ የምትወልደውን ዝይ አረድናት!!!››“Killing the Goose that laid the golden eggs.” ያለው ለዚህ ነበር፡፡ ወርቅ የምትጥለውን ዝይ እንድናርዳት ተገደድን:: ህዝቡ ዛሬ አንድ እንቁላል በ5 ብር ይገዛል፣ አንድ ዶሮ በ300 ብር ይሸምታል፡፡ ህወኃት/ኢህአዴግ መንግሥት ዶሮ ማርባት ያልቻለ መንግሥት ነው፡፡ በሃገሪቱ ዶሮና እንቁላል የፋብሪካ ምርቶች የሆኑ መስሎል፡፡ የተፈጥሮ ዶሮና እንቁላል ምርቶች ያላደጉባት ሃገር እንዴት በሁለት አሃዝ አደገች!!!፣ ሃገራችን በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ኢዱስትሪ መር ወደ ኢንዱስትሪ ተሸጋገርን ወደ መካከለኛው ገቢ ሃገራት በ2025 እኤአ እንደርሳለን እያሉ 8.4 ሚሊዩን ህዝብ ያስራበ መንግሥት ነው፡፡ የዓለም ዓቀፍ ፋይናንሻል ኢንስቲቱሽን የዓለም ባንክና አይኤም ኤፍ በተለይ በታዳጊ አገሮች ላይ ትልቅ ጫና በመፍጠር ፕራይቬታይዜሽን መርሃ-ግብር ከመንግስታዊ መዋቅር ማሻሻያ ፕሮግራም ዋነኛ አካል እንደሆነ ተሰበከ፡፡ በዚህም ምክንያት በብዙ ታዳጊ አገሮች የፕራይቬታይዜሽን ሽግግር በብቃት፣ በግልፅነትና ያለአድሎ ለማካሄድ አስፈላጊው ጊዜና ጥናት ባለመካሄዱ ከጅምሩ የተኮላሸ ለመሆን በቅቶል፡፡ በኢትዩጵያ ህወኃት/ኢህአዴግ የፖለቲካ ድርጅቶች በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በፕራይቤታይዜሽን ስም ንብረቶችና ኃብቶች ተቀራምተዋል፡፡ በሃገሪቱ ውስጥ የገበያ ውድድር ያለመኖር፣ የመዋለ-ንዋይ ፍሰት ደካማነት፣ የፋይናንሻል ሃብት እጥረትና የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚጫወተው ሚና ደካማነት ወዘተ ተደማምሮበት የፕራይቬታይዜሽን ሽግግር የተጨናገፈ ለመሆን በቅቶል፡፡ በኢትዬጵያ የፕራይቬታይዜሽን ሽግግርና ሂደት በቂ በሆነ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች፣ዲያስፖራና የባህር ማዶ ኢንቨስተሮች ባለመሳተፋቸው ምክንያትና፣በአክሲዩኖች ካፒታል ለተደራጁ ኢትዩጵያኖች እንዲሸጡ ባለመደረጋቸው አብዛኛዎቹ የመንግስት ኮርፖሬሽኖችንና ንብረቶች ባለቤትነትን ወደ ሜድሮክ ካንፓኒዎችና ኢፈርት ንብረትነት ማዘዋወራቸው የአደባባይ ሚስጢር ነው፡፡ የፕራይቬታይዜሽን የባህር ማዶ ኢንቨስተሮችን ያገለለና ያለ ነፃ ገበያ ውድድር የተቸበቸቡ የህዝብ ንብረቶች መሆናቸውን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት በኢትዬጵያ የተካሄደው የፕራይቬታይዜሽን ሽግግር የብዙ ሠራተኞች ቅነሳን ያስከተለ፣ ምርታማነትን የቀነሰ፣ ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን ያልጨመረ፣ መሆኑ በምጣኔ ኃብት ምሁራን ጥልቅ ጥናቶች ተረጋግጦል፡፡
በኢትዮጵያ የመለስ ዜናዊ ዘመን፣በመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ሙስና ሌብነት ተጀመረ!!!

ምንጭ፡- 1- Privatization and Public enterprises supervising agency and own competition.
*2- The author is graduate student at John Hopkins niversity. Email: ethiopia.capitalmarkets@gmail.com*

ለኦሮሞና ሱማሌ ህዝብ ግጭትን የጫሩ የህወኃት/ኢህአዴግ የጦር አበጋዞች ለፍርድ ይቅረቡ!!!
የህወኃት የጦር አበጋዞች መንግሥት የፈለፈለው የሱማሌ የጦር አበጋዞች መንግሥት ትጥቅ ይፍታ!!!
በዘር ፍጅት ተጠያቂዎች ለፍርድ ይቅረቡ!!!

## ኢት-ኢኮኖሚ ET-ECONOMY

### ‹‹የፕራይቬታይዜሽን››፣ የሆቴል ሚሊየነሮች!!!
### ‹‹ወርቅ የምትወልደውን ዝይ ገደልናት!!!››

(ክፍል ሁለት)

ፀ/ት ፂዩን ዘማርያም

<u>የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከናሽናላይዜሽን ወደ ፕራይቬታይዜሽን ሽግግር፡-</u>እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ከ1980 እስከ 2010 ዓ/ም የመንግስት ኮርፖሬሽኖችንና ንብረቶች ባለቤትነትን ወደ ግሉ ዘርፍ ንብረትነት ማዘዋወር በምዕራባዊያን አገራቶች አዛዥነት በዓለም ባንክና አይኤምኤፍ ጋሻ ጃግሬነት ዓለም ዓቀፋዊ ክስተት በመሆን በኢትዮጵያም ተፈፃሚ ሆኖል፡፡ በሃገራችን ውስጥ ከመንግስት ዘርፍ ወደ ግሉ ዘርፍ መተላለፍና መሸጥ ዋነኛ ምክንያቶች መኃል፣ የገንዘብ አያያዝ ብክነትና ሙስና በየግዜው እየጨመረ መሄድ፣ንብረቶቹን የማስተዳደር ብቃት ደካማነት በዚህም ምክንያት በየአመቱ የመንግስት ድጎማ እየተደረገላቸው በኪሳራ መስራታቸው የሚል ነበር፡፡ በዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ድርጅት ተቆምና በዓለም ባንክ ግዳጅና ተፅዕኖ የመንግስታዊ መዋቅር ስርዓት ማሻሻያ መርሃ-ግብር (structural adjustment program) ለማሻሻልና ለመቀየር የመንግስት ኮርፖሬሽኖችንና ንብረቶች ባለቤትነትን ወደ ግሉ ዘርፍ ንብረትነት ማዘዋወር ዋነኛው ምክንያት ሆነ፡፡ የዓለም ዓቀፍ ፋይናንሻል ኢንስቲቱሽን በተለይ በታዳጊ አገሮች ላይ ትልቅ ጫና በመፍጠር የፕራይቬታይዜሽን መርሃ-ግብር ከመንግስታዊ መዋቅር ማሻሻያ ፕሮግራም ዋነኛ አካል እንደሆነ ተሰበከ፡፡ በዚህም ምክንያት በብዙ ታዳጊ አገሮች የፕራይቬታይዜሽን ሽግግር በብቃትና በግልፅነት ለማካሄድ አስፈላጊው ጊዜና ጥናት ባለመካሄዱ የተኮላሸ ለመሆን በቅቶል፡፡ በክንውኑም የወያኔ የቢዝነስ ድርጅቶችና ጥቂት ከበርቴዎች ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ያደረገ ሆኖል፡፡ በመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በወታደራዊው መንግሥት የተወረሱ መንግስታዊ ድርጅቶችን ወደ ግሉ ዘርፍ በ1994 ዓ/ም በአዋጅ ለማዘወወር የተቆቆመ ድርጅት ዴሬክተር ጀነራል አሰፋ አብርሃ የመንግሥት ሆቴሎች ሽያጭ፣ በዝምድና በሙስና በጠባብ ዘረኝነት ስሜት አንዱን ለመጥቀም የወያኔ የንግድ ድርጅቶችንና ጥቂት ባለጸጎችን በፕራይቬታይዜሽን ስም ሚሊየነሮች ያደረጉት ሆቴሎቹን በርካሽ በመሸጥ ነበር፡፡ ዛሬ እነዚህ በርካሽ የተሸጡት የመንግሥት ሆቴሎች፣ ከመቶ እጥፍ በላይ ሊሸጡ እንደሚችሉ ልብ ይበሉ፡፡

የመንግስት የሆቴል ኢንተርፕራየዝ ሽያጭ ከ1994/95 እስከ 2003 ፕራይቬታይዝ የተደረጉ

<u>(List of Privatized Stat Owned Hotels Enterprises from 1994/95 up to March 2003)</u>

{1} <u>ራንዴቩ ካፍቴሪያ</u>[3] የመንግስት ሆቴል በ06/25/97 ዓ/ም፣ለወ/ሮ እንይሽ አስራት የተሸጠበት ዋጋ 2,800,000.00 ሚሊዩን ብር

{2} <u>አክሱም ሆቴል</u>[1] የመንግስት ሆቴል በ07/01/95 ዓ/ም፣ለኢትዩጵያ ትራቭል ኤክስፕሬስ የተሸጠበት ዋጋ 890,167.00 ሽህ ብር

{3} <u>ፎገራ ሆቴል</u>[2] የመንግስት ሆቴል በ07/03/00 ዓ/ም፣ ገዢ ጌትኮ ካንፓኒ( Geaitco.) የተሸጠበት ዋጋ 950,105.00 ሽህ ብር

{4} ወንዛዬ ሆቴል[1] የመንግስት ሆቴል በ09/11/95 ዓ/ም፣ አማራ ዲቨሎፕመንት አሳሴሽን የተሸጠበት ዋጋ 500,000 .00 ሺህ ብር

{5} ተራራ ሆቴል[4] የመንግስት ሆቴል በ12/02/95 ዓ/ም ፣ ገዢ አዲስ ፋና የተሸጠበት ዋጋ 617,480.92 ሺህ ብር

{6} ባህር ዳር ጊዩን[1] የመንግስት ሆቴል በ07/04/95 ዓ/ም፣ለፉአንግ ቢውልዲንግ ኮንትራክተር የተሸጠበት ዋጋ 1,100,000.00 ሚሊዩን ብር

{7} ጣይቱ ሆቴል[2] የመንግስት ሆቴል በ05/19/99 ዓ/ም፣ዘ የሎ ፔጅ ለአቶ ፍፁም ዘአቡ አስግዶም የተሸጠበት ዋጋ 5,273,000 ሚሊዩን ብር

{8} ግሸን ሆቴል(ጊዩን)@[2] የመንግስት ሆቴል በ07/19/99 ዓ/ም ፣ ገዢ ወ/ሮ ይህደጋ ገብረስላሴ የተሸጠበት ዋጋ 12,527.15 ሺህ ብር

{9} ራስ ሆቴል (ደብረዘይት)[1] የመንግስት ሆቴል በ09/04/96 ዓ/ም፣ ገዢ ሜድሮክ ኢትዩጵያ የተሸጠበት ዋጋ 8,027,302.23 ሚሊዩን ብር

{10} ራስ ግሪል[1] የመንግስት ሆቴል በ07/19/99 ዓ/ም፣ ገዢ አዲስ ፋና የተሸጠበት ዋጋ 229,993.20 ሺህ ብር

{11} ላሊበላ ሬስትቶራንት[1] የመንግስት ሆቴል በ09/26/95 ዓ/ም፣ ገዢ አይቤክስ ሆቴል የተሸጠበት ዋጋ 905,155.50 ሺህ ብር

{12} ጊዳቦ ሆቴል[1] የመንግስት ሆቴል በ12/01/95 ዓ/ም፣ ገዢ ወንዶ ገነት ፒኤልሲ የተሸጠበት ዋጋ 505,000 ሺህ ብር

{13} ጊቤ ኢትዩጵያ ሆቴል[1] የመንግስት ሆቴል በ9/13/1999 ዓ/ም፣ ገዢ አዲስ ፋና የተሸጠበት ዋጋ 475,999.55 ሺህ ብር

{14} ዋልጋ ኢትዩጵያ ሆቴል@[2] የመንግስት ሆቴል በ05/19/99 ዓ/ም፣ ገዢ ወ/ሮ በላይነሽና ሌሎች የተሸጠበት ዋጋ 426,135.39 ሺህ ብር

{15} ወሊጋ ኢትዩጵያ ሆቴል[4] የመንግስት ሆቴል በ12/01/95 ዓ/ም፣ገዢ አዲስ ፋና የተሸጠበት ዋጋ 517,047.23 ሺህ ብር

{16} ዳህላክ ፓራዳይዝ[1] የመንግስት ሆቴል በ07/06/95 ዓ/ም፣ገዢ ወ/ሪ ሬታ ፀሃይ የተሸጠበት ዋጋ 650,000 ሺህ ብር

{17} ቱሪስት ሆቴል[1] የመንግስት ሆቴል በ09/29/95 ዓ/ም፣ ገዢ ወ/ሪ አለምፀሃይ ተገኘወርቅ የተሸጠበት ዋጋ 1,100,000 ሚሊዩን ብር

{18} ብሉ ናይል ራስ ሆቴል[1] የመንግስት ሆቴል በ07/05/2002 ዓ/ም፣ ገዢ ቤተዛታ ሄልዝ ስርቪስ የተሸጠበት ዋጋ 6,501,100 ሚሊዩን ብር

{19} ወሊሶ ኢትዩጵያ ሆቴል[1] የመንግስት ሆቴል በ03/26/2003 ዓ/ም፣ለወ/ሮ ዝምታወርቅ ነጋሽ የተሸጠበት ዋጋ 1,600,000 ሚሊዩን ብር

{20} አምቦ ኢትዩጵያ ሆቴል[1] የመንግስት ሆቴል በ4/8/2003 ዓ/ም፣ ገዢ አቶ ታከለ ታደሰ የተሸጠበት ዋጋ 2,623,200 ሚሊዩን ብር

{21} ዋቢሸበሌ ሆቴል ሃዋሳ ቁ1[5] የመንግስት ሆቴል በ3/4/2005 ዓ/ም፣ለዩናይትድ አፍሪካን ግሩፕ የተሸጠበት ዋጋ 6,950,000 ሚሊዩን ብር

{22} ጋምቤላ ኢትዩጵያ ሆቴል[1] የመንግስት ሆቴል በ21/7/2005 ዓ/ም፣ ገዢ ሳውዝ ዌስት ፒኤልሲ የተሸጠበት ዋጋ 3,750,000 ሚሊዩን ብር

{23} ቀEራ ጊዩን ሆቴል (ጎንደር)[2] የመንግስት ሆቴል በ6/8/2005 ዓ/ም፣ ለሲጂኤፍ ቢዝነስ ግሩፕ የተሸጠበት ዋጋ 3,322,000 ሚሊዩን ብር

{24} ሆቴል ዲ አፍሪክ @[3] የመንግስት ሆቴል ቀንና ዓ/ም ያልተገለፀ፣ለአቶ ስይፉ ገብረዩሃንስ የተሸጠበት ዋጋ 6,500,000 ሚሊዩን ብር

{25} ድሬዳዋ ራስ ሆቴል ቁ2[2] የመንግስት ሆቴል በ24/6/2008 ዓ/ም፣ ገዢ አቶ ኢዬብ ምህረት የተሸጠበት ዋጋ 5,001,919.00 ሚሊዩን ብር

{26} ድሬዳዋ ራስ ሆቴል ቁ1[2] የመንግስት ሆቴል በ9/5/2008 ዓ/ም፣ ገዢ አቶ በላይነህ ተስፋዬ የተሸጠበት ዋጋ 11,041,916.40 ሚሊዩን ብር

{27} ሃረር ራስ ሆቴል[2] የመንግስት ሆቴል በ15/11/02 ዓ/ም፣ ገዢ ወ/ሮ ገነት አበራ የተሸጠበት ዋጋ 11,245,120.75 ሚሊዩን ብር

{28} ጎሃ ሆቴል[2] የመንግስት ሆቴል በ25/6/2009 ዓ/ም፣ ገዢ ቤታስ ኢንዱስትሪ ፒኤልሲ የተሸጠበት ዋጋ 20,000,116 ሚሊዩን ብር

{29} ጣና ጊዩን ሆቴል የመንግስት ሆቴል በ3/5/2009 ዓ/ም፣ ገዢ ብሉ ናይል ሪዞርት ሆቴል የተሸጠበት ዋጋ 42,000,000 ሚሊዩን ብር

{30} ባሌ ጎባ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል[2] የመንግስት ሆቴል በ8/7/2009 ዓ/ም፣ለገድብ ኢንጅነሪንግ ፒኤልሲ የተሸጠበት ዋጋ 7,500,000 ሚሊዩን ብር

{31} ላሊበላ ሮሃ ጊዩን[2] የመንግስት ሆቴል በ25/9/96 ዓ/ም፣ለአጂካ ትሬዲንግ ኤንድ ትራቨል የተሸጠበት ዋጋ 22,001,000 ሚሊዩን ብር

{32} የሃ ጊዩን ሆቴል[2] የመንግስት ሆቴል በ8/8/2009 ዓ/ም፣ ገዢ ቢቲ አድቨርት ፒኤልሲ የተሸጠበት ዋጋ 21,000,027 ሚሊዩን ብር

{33} ሮሃ ጊዩን ሆቴል[2] የመንግስት ሆቴል በ2/11/2010 ዓ/ም፣ ገዢ አያት ሼር ካንፓኒ የተሸጠበት ዋጋ 31,640,799 ሚሊዩን ብር

{34} ናሽናል ሆቴል[2] የመንግስት ሆቴል በ29/08/02 ዓ/ም፣ ገዢ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተሸጠበት ዋጋ 17,406,880.24 ሚሊዩን ብር

{35} ቦኩ ሳፐ[1] የመንግስት ሆቴል በ8/7/1995ዓ/ም፣ ገዢ ዲንሾ ኦሮሚያ የተሸጠበት ዋጋ 210,231ሺህ ብር

{36} ጂማ ኢትዩጵያ ሆቴል@[2] የመንግስት ሆቴል በ3/30/2001ዓ/ም፣ለቀኛዝማች ተካ ኢገኖ የተሸጠበት ዋጋ 611,432.40ሺህ ብር

አጠቃላይ የሆቴል ኢንተርፕራይዞች ሽያጭ 246,558,352.70 ሚሊዩን ብር ነበር፡፡

የሽያጩ ዓይነት (Type of sale) ¹የቢዝነስ ሽያጭ፣(Business sale)፤² የንብረት ሽያጭ፣(Sale of asset)፤³ (አጠቃላይ ሽያጭ ቢዝነሱንና ህንፃውን)፤
⁴ ቢዝነስ/ኤምኢቢኦ፣ Business / Management/Employee Buyout (MEBO)፤ለማነጅመንትና ለሠራተኛ የተሸጠ ሆቴል ⁵ Joint venture፤አሽሙር ንግድ
@ These are properties returned to former owners in accordance with Proclamation No. 110/1995.
Source: Privatization and Public enterprises supervising agency and own competition.

{1} በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ለቀድሞ የሆቴል ባለቤቶቻቸው የተመለሱ ሆቴል ዲ አፍሪክ ለአቶ ሰይፉ ገብረዮሃንስ፣ ግሸን ሆቴል ጊዮን ለወ/ሮ ይህደጋ ገብረስላሴ፣ ዋልጋ ኢትዮጵያ ሆቴል ለወ/ሮ በላይነሽ፣ ጂማ ኢትዮጵያ ሆቴል ለቀኛዝማች ተካ ኢገኖ ንብረታቸው ተመልሶል፡፡

{2} የመንግሥት ፓርቲዎች ንብረት Government Party property
የመንግሥት ፓርቲዎች ንብረት ከመንግሥት ሆቴል ኢንተርፕራየዝ ሽያጭ፣ዋንዛዬ ሆቴልን የአማራ ልማት ማህበር፣ ናሽናል ሆቴልን የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን፣ ቦኩ ሳፓ ዲንሾ ኦሮሚያ እንዲሁም በአዲስ ፋና ማናጅመንትና ሠራተኞች የተሸጡ ሆቴሎች፣ ተራራ ሆቴል፣ ራስ ግሪል፣ ጊቤ ኢትዮጵያ ሆቴልና፣ ወለጋ ኢትዮጵያ ሆቴል ይገኙበታል፡፡ የአዲስ ፋና ጀነራል ማርቸንዳይዝ ኤንድ ሆቴልስ ትሬድ ሼር ካንፓኒ፣ የፋይናንስ ማናጀር አቶ አስራትወርቁ ሃይሌ ከሚል መረጃ በስተቀር ስለ አዲስ ፋና ኮንፓኒ ታሪክ፣ሹር ሆልደርስ ባለቤቶች የሚገለፅ ነገር ሁሉ ድብቅ ነው፡፡ የህወኃት/ኢህአዴግ የፖለቲካ ፓርቲዎች የንግድ ድርጅት መሆኑ እውን ነው፡፡

{3} ሜድሮክ ኢትዮጵያ Midroc Ethiopia
የሜድሮክ ኢትዮጵያ ባለቤት ሼህ መሃመድ አላሙዲን ከህወኃት የመንግሥት ሆቴል ኢንተርፕራየዝ ሽያጭ፣ በፕራይቬታይዤሽን ስም ከተቀራመቱት የቅርጫ ድርሻ አንደኛው መስቀል አደባባይ የሚገኘው ራንዴቩ ካፍቴሪያ በሚስታቸው ወ/ሮ እንይሽ አስረስ በሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሽህ ብር የተሸጠላቸው ንብረት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ደብረዘይት የሚገኘው ራስ ሆቴል በስምንት ሚሊዮን ስባት መቶ ሽህ ብር በርካሽ ዋጋ የተቸበቸበው የህዝብ ንብረት ይጠቀሳሉ፡፡

{4} እቴጌ ጣይቱ ሆቴል Taitu Hotel
በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመን፣ በመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በደርግ አገዛዝ ስርዓት የተወረሱ መንግስታዊ ድርጅቶችን ወደ ግሉ ዘርፍ ለማዘወወር በ1994 ዓ/ም በአዋጅ የተቋቋመ ድርጅት ዴሬክተር ጀነራል አሰፋ አብርሃ (ስዬ አብርሃ ወንድም) 05/19/99እኤአ ለእህታቸው ባል አቶ ፍፁም ዘአቡ አስግዶም እቴጌ ጣይቱ ሆቴል በአምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ሽህ ብር (5,273,000 ) ሸጡላቸው፡፡ በኢትዮጰያ የመጀመሪያ የሆነውን ጥንታዊ ሆቴል የሃገር ሃብትና ቅርስ ሆኖ ሳለ በህወሃት/ኢህአዴግ ታሪክን የማጥፋት የቆየ ደመኝነት ለዘመዳቸው እንዲሸጥ ተደረገ፡፡ ገዥው 35 በመቶ 1,845,550 ብር ከፍለው ቀሪውን 3,427,450 ብር በአምስት አመታት ውስጥ በአመት 685,490 ብር እየከፈሉ ለመጨረስ ተስማምተው ቅርሱን በእጃቸው አስገቡ፡፡ እቴጌ ጣይቱ ሆቴል ጥር 3 ቀን 2007 እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ109 አመቱ በእሳት ተቃጠለ፡፡

አቶ ፍፁም ዘአቡ አስግዶም፣ በመለስ ዜናዊ ውርስና ቅርስ የሆነው የሙስና ፋብሪካ ምርት አምራች ዴሬክተር ጀነራል አሰፋ አብርሃ (ስዬ አብርሃ ወንድም) 05/19/99እኤአ ለእህታቸው ባል አቶ ፍፁም ዘአቡ አስግዶም፣ከሸጡላቸው ውስጥ፡-
{1}እቴጌ ጣይቱ ሆቴል በአምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ሽህ ብር (5,273,000 ) ሸጡላቸው፡፡
{2}የጉለሌ የሳሙና ፋብሪካ በ12/23/1996 አ/ም በ22,370,000 (በሃያ ሁለት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሰባ ሽህ ብር) ገዝተዋል፡፡{3}ሐረር ፕሪንቲንግ ኢንተርፕራይዝ ማተሚያ ቤትን በ1,164,000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ስድሳ አራት ብር) በ10/18/1995 ዓ/ም ገዝተዋል፡፡ በጥናት እንደተረጋገጠው በኢትዮጵያ አይን ያወጣ ሙስና ሌብነት የተጀመረው በመለስ ዜናዊ ፊት አውራሪነት በህወኃት፣ በብአዴን፣ ኦህዴድ፣ ደህዴግ፣ ወዘተ ዘመን አገዛዝ ሲሆን፣ይህውም በ1994 ዓ/ም አዋጅ መነሻነት ከመንግሥታዊው ዘርፍ ወደ ግሉ ዘርፍ ለማዘወወር በተቋቋመው ድርጅት «የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ» ዴሬክተር ጀነራል አሰፋ አብርሃ አማካኝነት የህዝብ ሃብት የተሸጠበት ጊዜ ነበር፡፡ በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመን፣የመንግሥት እርሻዎች፣ ፋብሪካዎች፣ ሆቴሎች ወዘተ ተሸጡ፣ የከተማ መሬት በሊዝ ስም ተሸጡ፣ የገጠር መሬት ለኢንቨስተሮች ተሸጡ!!! ብሎም የትግራይን ክልል ድንበር ማስፋት ተያያዙት!!! የትግራይን ህዝብ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለማጣላት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ በህግ ስም! በአዋጅ ሰም! ዘረፋ ህጋዊነት እንዲያገኝ ተደረገ፡፡ ዛሬ የምናያቸው ሃብታሞች ትላንት ቁምጣ አድርገው፣ ሽበጥ ተጫምተው፣ ቦንብ ታጥቀው፣ ክላሽ ደግነው በጉልበት ያስገበሩን ወራሪዎች የሃገሩን ኃብት ገና ዘርፍው አልጠገቡም!!! ቪላ ቤት ሰሩ አልጠገቡም፣ ፎቅ ገነቡ አልጠገቡም! ሚሊዮነር ሆኑ አልጠገቡም! መቼም አይጠግቡም፡፡ ስለዚህ ታግሎ ከመንቀል ሌላ መፍትሄ የለም!!! እነዚህን የመንግሥት ሆቴሎች፣ እርሻዎችና፣ ፋብሪካዎች በቀጣይነት እንዘግባለን፡፡ የተደረገውን ዘረፍ የሚያውቁ ሁሉ ለመጻፍ አይስነፉ፣አይፍሩም ለነገው ትውልድ የኃብቱ ምንጭ በዘረፋ የተገኘ መሆኑን ምስክርነታችንን ማቆየት ግድ ይላልና!!!
የኢትዩጵያ ኢኮኖሚ ኃላቀር በመሆኑ ነፃ የገበያ ውድድር ያለመኖር፣ የመዋለ-ንዋይ ፍሰት ችግር፣ የፋይናንሻል ሃብት እጥረትና የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚጫወተው ሚና ደካማነት ወዘተ ተደማምሮበት የፕራይቬታይዜሽን ሽግግር የተጨናገፈ ለመሆን በቅቶል፡፡ በኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ሽግግርና ሂደት በቂ በሆነ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች፣ ዲያስፖራዎች እንዲሁም የባህር ማዶ ኢንቨስተሮች ባለመሳተፋቸው ምክንያት አብዛኛዎቹ የመንግስት

ኮርፖሬሽኖችንና  ንብረቶች ባለቤትነትን ወደ ሜድሮክ ካንፓኒዎችና ኢፈርት ድርጅቶች በሙስና፣ በአድሎና በዝምድና አሰራር ንብረቶቹ  ማዘዋወራቸው ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ የፕራይቬታይዜሽን ክንውን የባህር ማዶ ኢንቨስተሮች ያገለለ፣ ያለ ገበያ ውድድር የተቸበቸቡ፣ በመሆኑ ውጤቱም የብዙ ሠራተኞች ቅነሳን ያሰከተለ፣ ምርታማነትን የቀነሰ፣ ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን ያልጨመረና፣ የህዝብ ኃብት ለጥቂት የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ብቻ እንደሸጡ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡

ምንጭ
Source: Privatization and Public enterprises supervising agency and own competition.

ለኦሮሞና ሱማሌ ህዝብ ግጭትን የጫሩ የህወኃት/ኢህአዴግ የጦር አበጋዞች ለፍርድ ይቅረቡ!!!
የህወኃት የጦር አበጋዞች መንግሥት የፈለፈለው የሱማሌ የጦር አበጋዞች መንግሥት ትጥቅ ይፍታ!!!
በዘር ፍጅት ተጠያቂዎች ለፍርድ ይቅረቡ!!!